በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም አሰራር ለመወሰን በወጣው ደንብ ቁጥር 181/2012 በአንቀጽ ሰባት የተዘረዘሩ የተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. አግባብነት ካላቸው አካላት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ቦርድ አባላትንና ሰብሳቢን እንዲሁም የየተጓደሉ ቦርድ አባላት እና ሰብሳቢን ከክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጋር በመምከር ይሰይማል፤
2. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅድ መያዛቸውን ያረጋግጣል፤ ዕቅዶቹን ያፀድቃል፤ አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል፤ ይከታተላል፤ ይገመግማል፤ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤
3. የልማት ድርጀቶችን ሒሳብ የሚመረምር የውጪ ኦዲተር ይሰይማል፤ የውጪ ኦዲት ሪፖርቶችን ያፀድቃል፤ በኦዲት ግኝቶች ላይ የእርምት እርምጃ መወሰዱን ይከታተላል፤
4. የመንግስት የልማት ድርጅቶች አፈፃፀም እና ተወዳዳሪነት እንዲሻሻል ለማድረግ ዘመናዊ የኮርፖሬት አስተዳደርና ኮርፖሬት ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፤
5. የልማት ድርጅቶችን መነሻ ካፒታል፤ የድርጅቶች ካፒታል እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ምክረ ሃሳብ ለመስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
6. የመንግስት የልማት ድርጅቶች አስፈላጊ ችሎታ፤ ልምድ እና ዕውቀት ባላቸው ሰዎች የሚመሩበትን ሥርዓት ይዘረጋል ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤
7. በክልሉ መንግስት አጠቃላይ አመራርና አቅጣጫ በመምራት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል እንዲዛወሩ የአሠራር ሥርዓት የሚዘረጋበት አግባብ ለመስተዳድር ምክር ቤት ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፤ ሲወሰንም ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ እንዲሆንም ያደርጋል፤
8. አስፈላጊ ሲሆን በሥሩየሚገኙ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እንዲፈርሱ ከሌላ ድርጅት ጋር እንዲዋሃዱ፤ እንዲሸጡ ወይም እንዲከፋፈሉ ለመስተዳድ ምክር ቤት ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፤ ሲፈቀድ ተፈፃሚነቱን ይከታተላል ያስፈፅማል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

9. የትርፍ ድርሻ ክፍፍል ሥርዓት ያዘጋጃል፤በቦርዱ በሚቀርብለት ሃሳብ መሠረት ከተጣራ ትርፍ በየበጀት ዓመቱ ከልማት ድርጅቶች ለመንግስት ስለሚከፈል የትርፍ ድርሻ ክፍያ መጠንለመስተዳድር ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፤ሲወሰንምተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

10.የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሂሳብ ከመዝገብ መሰረዝን በሚመለከት ለመስተዳድር ምክር ቤት ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

11.የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የፋይናንስ አጠቃቀማቸውን፣ የብድር አወሳሰድና አመላለሳቸውን በቅርበት ይከታተላል፤

12.የመንግስት የልማት ድርጅቱን የተፈቀደ ካፒታል በዚህ ደንብ አንቀፅ18(2) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ በሙሉ ተከፍሎ እንዲያልቅ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ የመጠባበቂያ ሂሳቦች እንዲያዙ ወይም ከመንግስት ገንዘብ እንዲመደብ ለመስተዳድር ምክር ቤት ምክረ ሀሳብ ያቀርባል ሲወሰንምተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

13.የመንግስት የልማት ድርጅቶች ለምርምር እና ለፈጠራ በቂ በጀት እንዲመድቡ እንዲሁም የተገኘውን የምርምር እና የፈጠራ ውጤት የሚመለከተው አካል ለዚህ ተግባር ያስቀመጣቸውን አሰራር ተከትሎ እንዲያሰራጩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

14.የመንግስት የልማት ድርጅቶችን አፈፃፀም እና ሁኔታ የሚያሳዩ የመረጃ ሥርአት ያደራጃል፤ ማዕከላዊ አስቀማጭም ሆኖ ያገለግላል፣ የድርጅቶችን አፈፃፀም የሚመለከቱ የወል መረጃዎችን ያሳውቃል፤

15.ለመንግስት የልማት ድርጅቶች ቦርድ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ዋና ሥራ አስኪያጅ እና ምክትል ስራ አስኪያጆች ቅጥር እና ስንብት ውሳኔ ከድርጅቶች ቦርድ ሲቀርብለት ከክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጋር በመምከር መርምሮ ያፀድቃል፤

16.የልማት ድርጅቶች ተሞክሮ የሚለዋወጡበትን መድረክ ያዘጋጃል፣ የድርጅቶቹን የአመራር አቅም ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥልጠናዎች እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

17.ከሕግ አግባብ ውጪ የተወሰዱ ንብረቶችን እና በእንጥልጥል ያሉ ጉዳዮችን በሥራ ላይ ባሉና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት አጣርቶ ውሳኔ ይሰጣል፤

18.በመንግስት የልማት ድርጅቶ ውስጥ መንግስት ያለውን የባለቤትነት መብት ለማስከበር የሚያስፈልጉ ተግባሮችን ለማከናወን የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

19.የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን የሥጋት ሥራ አመራር ሥርዓት ያዘጋጃል፤ እንዲሁም የግምገማና የማበረታቻ አፈፃፀም አሠራር ሥርዓት ያዘጋጃል፤

20. የመንግሥት ልማት ድርጅቶች የመንግስት የልማት ፖሊሲወች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለማረጋገጥ ከሚመለከተው አካል ጋር ይመክራል፤ ክትትልም ያደርጋል፤

21.የመንግስት ልማት ድርጅቶች በልዩ ሁኔታ ትርፋቸውን እንዲጠቀሙ ወይም ለማስፋፍያ እንዲያውሉ የሚያስችላቸውን የአሰራር ስርዐት ይዘረጋል፤

22.የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ኪሳራ ሲያጋጥማቸው ምንጩን በጥናት በመለየት፤ አዋጭ የሆነ የወጪ ቅነሳ ሥርዓት አዘጋጅቶ ለመስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፤

23.የመንግሥት ልማት ድርጅቶች የአጭር እና የረጅም ጊዜ ብድር ከባንክ የሚያገኙበትን የአሰራር ስርዓት አጥንቶ ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

24.የልማት ድርጅቶቹ የፋይናንስ አሠራር ሥርዓት በተለይም ገንዘብና ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን ያዘጋጃል ወይም ይዘረጋል። የልማት ድርጅቶቹን ውጤታማነት ይበልጥ ለማረጋገጥ የሚያስችል እና የሥራ ባህሪያቸውን ያገናዘበ ልዩ ልዩ መመሪያዎችን ያወጣል፤

25.የባለስልጣኑን ዓላማ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

የባለስልጣኑ አወቃቀር

በአንድ ዋና ሃላፊ እና ምክትል ሃላፊ ፣በሁለት ዳይሬክቶሬት ማለትም

1ኛ.የኮርፖሬት ፋይናንስና ፈንድ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በስሩ

1.1.የኮርፖሬት ፋይናንስ ፈንድ አስተዳደርና ክትትል ቡድን

1.2. የፋይናንስ፣ግዥና ንብረት አስተዳደር ቡድን

2ኛ.ጥናት፣ዕቅድ፣ክትትል፣ድጋፍና ግምገማ ዳይሬክቶሬት በስሩ

2.1.ጥናትና አቅም ግንባታ ቡድን

2.2.ዕቅድ ፣ክትትል፣ድጋፍና ግምገማ ቡድን

ይዞ የተደራጀ ሲሆን ለግዜው በሁለት ዳይሬክቶሬቶች እና በአራት ዓላማ ፈፃሚ ፣ሦስት ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎችን ጨምሮ በድምሩ በ9 ሰው ሃይል ስራውን እያንቀሳቀሰ ይገኛል።